በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 13
# የመጨረሻ ክፍል

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

***<u>ቦታ፡-</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ግንቦት ፳፪ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13

**መተው**

- አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ ነገሮችን የምንመለከትበትን ወይም የአግባቦት መንገዳችንን መቀየር ብንችል ይህ መንገዳችን ግትርነት የሌለን መሆናችንንና መተው መቻላችንን ይገልጻል፡፡
- ይህም የራሳችንን ፍላጎት ስለሌላው አሳልፎ ለመስጠት ያለንን ዝግጁነት የሚጠቁም ነው፡፡
- የዚህም አቅጣጫ ተቃራኒው ግትርነት ወይም ድርቅና ሲሆን በትዳር ውስጥ የግጭት መንሥኤ ነው፡፡
- ዛሬ ይህን የመሰለው የመተው ወይም የመቀባበል ሕይወት በበርካታ ወጣቶች ዘንድ እየተዘነጋ ነው፡፡
- ይህን ዓይነት ሕይወትም የደካማነትና የጉድለት ምልክት ሆኖ የሚቆጠር ሲሆን በራስ ሐሳብ ሁል ጊዜ ግትር ሆኖ መገኘትም የራስን ጠንካራ ጎን ማሳያ ምልክት ሆኖ ይታሰባል
- ነገር ግን በተደጋጋሚ የተሰጠን ምክር ‹‹ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፡፡ ›› ***ቀዳ ጴጥ 5፡5፡፡*** የሚል ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13

## መተው

- መተው ለባልም ሆነ ለሚስት ብሎም ለልጆችም አስፈላጊ ምግባር ነው፡፡ ስለዚህ እንዴት መተው እንደምንችል ወይም የራሳችንን ፍላጎት በቅድሚያ ለጌታችን ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ በማስከተልም ለባልንጀሮቻችን፣ ለትዳር አጋራችን፣ ለምንኖርባት አገር ሕግ፣ ለልጆቻችንም ሳይቀር አሳልፎ መስጠት የሚያስችሉንን ብልሃቶች መማር ያስፈልገናል፡፡
- መተው የደካሞች ሳይሆን የብርቱ ሰዎች መታወቂያ ምልክት ነው፡፡
- በክርስቶስ ብርታትን ያገኙ ሁሉ በነገሮች አሸናፊ ሆነው ለመገኘት ሲሉ በፈቃዳቸው ሲተው እናገኛቸዋለን፡፡
- መተው የራስን ፍላጎት፣ ምኞች አመለካከት ስለሌላው ሲሉ መተው ስለሆነ የፍቅር ምልክት ነው፡፡
- መተው የብዙዎችን ቤት የታደገ ሲሆን … ግትርነት ግን የበርካታዎችን ትዳር አፍርሷል፡፡
- መተው በይበልጥ በሚስት በኩል ተፈላጊ ነው፡፡ ‹‹ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ፡፡ ›› ኤፌ 5፡24፡፡
- ይሁን እንጂ ባሎችም ለሚስቶቻቸው ምኞትና ተስፋ ራሳቸውን ለመስጠት የተዘጋጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13

**መተው**

- መተው በርካታ ሥልጠናዎች የሚያስፈልጉት ሲሆን በቤተክርስቲያንም ሆነ በቤታችን ከልጅነት ጀምሮ አብሮ ሊያድግ የሚገባው ምግባር ነው።
- የራሳቸውን ፍላጎት ለእግዚአብሔር፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለወላጆቻቸውና ለመምህራኑ አሳልፈው መስጠት የሚችሉ ወንዶች ወጣቶችና ልጃገረዶች ከራሳቸው ይልቅ ለትዳር አጋራቸው ፍላጎትና ምኞት መሳካት ቅድሚያ ይሰጣሉ።
- መተው የሚችሉ ሰዎች ለሌላው ቅድሚያ በመስጠታቸው የተነሳ ከፍተኛ ደስታና እርካታን ያገኛሉ።
- ነገር ግን ለመተው ፈቃደኝነት የሚታይበትን ወገን በጎ አቀራረብ ያለልክ የመጠቀምም ሆነ የሚጎዳ ድርጊት የመፈጸም አቅጣጫን በመከተል ሌላውን መበደል ግን አልተፈቀደም።
- ይህ መሰል አካሄድ በመተው የሚራመደውን ሰው ምንም ዓይነት መልካም ዕድል እንዳልተሰጠው በመቁጠር በድንገት እንግዳ ባሕርያት እንዲታዩበት ወይም የነርቮች መጎዳት እንዲያጋጥመው ብሎም ወደ ጭንቀትና የሕይወት ቀውስ ውስጥ ወደ መግባት ሊያደርሰው ይችላልና።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13

## መተው

- ባሎች ሆይ! ሚስቶች የራሳቸውን በመተው ለእናንተ ፍላጎት ያሳዩትን ተገዢነት በማየት አትመኩ፡፡ ምክንያቱም ይህን ዓይነቱን በጎ ሕይወት ባልመቀባበል የተነሳ መሰለቻቸትም ሆነ በመካከሉም በድንገት መሰበር ሊያጋጥም ይችላልና፡፡ ‹‹እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው፡፡›› ***ቀዳ ጴጥ 3፡7፡፡***
- ሚስቶች ሆይ! ባሎች የምትፈልጉትን ሁሉ በማሟላታቸው ወይም ይደረግላችሁ ዘንድ የምትጭኑትን ሁሉ በማድረጋቸው ደስ አይበላችሁ፤ በክርስቶስ የሆነ ትዳር መላ ሕይወት ይህ አይደለምና፡፡ ምክንያቱም ባሎች ሊሰላቹና ሊተዋችሁም ይችላሉና፡፡ ‹‹እንዲሁም፥ እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥ በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው፡፡›› ***ቀዳ ጴጥ 3፡1፡፡***
- ባለትዳሮች ሆይ ማንኛውንም ነገር እርስ በርስ ሳትመካከሩ በራሳችሁ ብቻ አትወስኑ፤ ሕወታችሁ ‹‹በክርስቶስ አንድ ስለሆነ›› በሕይወታችሁ በእያንዳንዱ ጉዳይ የምትሉት እንዲኖር መብት እንዳላችሁ አስተውሉ፡፡
- በዚህም አካሄድ ‹‹የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር…›› ***ካል ቆሮ 13፡14፡፡*** ይሆናልና፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13</u>

## ደስታ

- እግዚአብሔር ሰውን የፍጥረታት ገዢ እንዲሆን ፈጥሮታል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው፡፡ … አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ያው ሆነ፡፡›› ***<u>ዘፍጥ 2፡15-20፡፡</u>***
- እግዚአብሔር አምላክም ለአዳም የምትመቸው ረዳት ፈጠረለት፡፡ ‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት፡፡ እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረገ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ያው ሆነ፡፡ አዳምም ለእንስሳት ሁሉ፥ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ፥ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር፡፡ እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው፡፡ እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት፡፡›› ***<u>ዘፍጥ 18-22፡፡</u>***
- እግዚአብሔርም ይህን ሕይወት በደስታ እንዲኖሩ ሰጣቸው፡፡ ‹‹ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡፡›› ***<u>ዘፍጥ 2፡24፡፡</u>***

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13

## ደስታ

- ነገር ግን አዳምና ሔዋን የደስታቸው ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር በድለው መለየታቸው የሚያሳዝን ነበር፡፡ በበደላቸውም ምክንያት በገነት የነበረውን ደስታና ከእግዚአብሔርም ሆነ እርስ በርሳቸውም ያስተሳሰራቸውን የተቀደሰ አንድነት አጡ፡፡
- ከመበደላቸውም አስቀድሞ ያልተሰማቸውም ስሜት ‹‹አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፥ አይተፋፈሩም ነበር፡፡›› *ዘፍጥ 2፡25፡፡* ከበደሉ በኋላ ተሰማቸው፡፡ ‹‹የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፥ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ፡፡›› *ዘፍጥ 3፡7፡፡* ይህ ሁሉ ሰው ከእግዚአብሔር ውጪ ሊያገኘው ፈልጎት በነበረው የደስታ ፍላጎት የተከሰተ ነው፡፡
- በእግዚአብሔርና በአዳም መካከል የነበረው ንግግር ልዩና የሚያስደንቅ ነበር፡፡ እግዚአብሔር አዳም እንደበደለ ተረድቶ ከርሱ ሲደበቅ አይቶ የት እንደሆነ ጠየቀው፡፡ አዳምም ‹‹በገነት ድምፅህን ሰማሁ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም፡፡›› አለ፡፡ *ዘፍጥ 3፡10፡፡*
- አዳም ይህ ከበደለ በኋላ የተሰማው ስሜትም ሆነ የተጠቀመው ቃል፤ አስቀድሞ ተሰምቶትም ሆነ ተናግሮት የሚያውቀው አልነበረም፡፡ እነርሱም ‹‹ፍርሐት፣ ራቁትነትና መደበቅ›› ሲሆኑ ከመበደሉ በፊት የኖረበት ሕይወት ተቃራኒዎች ነበሩ፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13

## ደስታ

- እግዚአብሔር ‹‹ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን?›› ***ዘፍጥ 3፡11*** በማለቱ ንግግራቸው ቀጥሎ ነበር፡፡
- እግዚአብሔር ሰው በመበደሉ የተነሳ የማፈር፣ የመፍራት ወዘተ ተቃራኒ ስሜቶች ወደ ዓለም መግባት መጀመራቸውን ተመልክቷል፡፡
- ነገር ግን ጌታችን አምላካችን በበደልን ጊዜ የተውናቸውን በጎ ስጦታዎች ሁሉ ሊመልስልን ወደዚህ ዓለም በመምጣት አድኖናል ኀፍረታችንንም አርቆልናል፡፡
- ጌታችን በምድር ‹‹ደስታችንን›› ብሎም ሰማያዊ ሐሴታችንን የሰረቀብንን የኃጢአትና የክፋት ኃይል ያሸንፍልንና ዕዳችንን ይከፍል ዘንድ በመስቀል ላይ ስለኃጢአታችን ተሰቅሎ ሞቶልናል፡፡
- ጌታችን ሲወለድም ወዲያውኑ መላእክት ‹‹ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ…›› ***ሉቃ 2፡14፡፡*** እያሉ ዘምረዋል፡፡
- አዳምና ሔዋን በገነት የነበራቸው የመጀመሪያው ደስታ እንደተመለሰ ለማረጋገጥም ጌታችን የመጀመሪያውን ተአምር በቃና ዘገሊላ የሠርግ ቤት አድርጓል፡፡ ***ዮሐ 2፡1-11፡፡***
- በክርስቶስ አንድ የሚሆኑ ባለትዳሮችም በተቀደሰው አንድነት በገነት እንደነበረው በደስታ ይኖራሉ፡፡በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው ምስጢረ ተክሊል የሚሠራው ይህንኑ ነው፤ በምስጢሩ አማካኝነት ተጋቢዎቹ በክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ሲጋቡ አንድ አካልና አንድ መንፈስ ይሆናሉ፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13

## ደስታ

- ስለዚህ በሥነ ፍጥረት አስቀድሞ በእግዚአብሔር የታቀደውንና በኋላም በማዳኑ የተመለሰልንን ደስታ ለመጎናጸፍ አንዱና ብቸኛው መንገድ ጋብቻችንን/ትዳራችንን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ ማድረግ ነው፡፡
- ለአንዳንድ ባለትዳሮች ብቸኛ ገጽታ ያለው ይህን ደስታና ሰላም መጎናጸፍ የሚከብዳቸው ጋብቻቸው/ትዳራቸው ከክርስቶስ ውጪ ስለሆነ ነው፡፡ ለምሳሌ አንዱ ኦርቶዶክሳዊ የተዋሕዶ ክርስቲያን ቢሆን ሌላው ባይሆን ይህ ደስታ አይኖርም፤ ከጋብቻቸው በፊት በሃይማኖታቸው (ከምስጢራቱም በመሳተፍ) አንድ መሆን ይጠበቅባቸዋልና፡፡
- ምናልባት ስሜታዊ፣ ቁሳዊ ወይም የችሎታዎች ባለጠግነት ሊኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን በክርስቶስ በሆነ ትዳር የሚገኘውን ፍጹም ሰላምና ደስታ ግን ፈጽመው ሊጎናጸፉ አይችሉም፤ እነዚህ ፍሬዎች የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ናቸውና፡፡ እነርሱም ‹‹ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት።›› *ገላ 5፡22-23፡፡* ናቸው፡፡
- ይህንም የተቀደሰ ሕይወት አንድ ሊሆኑበትና ደስ ሊሰኙበት የሚችሉት በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተጠምቀው የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በምስጢረ ሜሮን በኩል የተቀበሉ ወንድና ሴት ብቻ ለመሆን የቻሉበትም ምክንያት ይኸው ነው፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13</u>

## ደስታ

- የተወደዳችሁ ልጆቻችን ምዕመናን! የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች በእኛ ውስጥ እንዳሉ እናስተውልና፤ መንፈሱን ከ‹‹ማዳፈን - ማጥፋት›› ይልቅ ‹‹ማቀጣጠል - ማፋፋም›› እንድንችል ጠንክረን መሥራት ይገባናል፡፡
- ስለዚህ ተከታታይነትና ቀጣይነት ባለው ጸሎት፣ ጾም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ ትርጓሜያቱንም በማጥናት፣ አግልግሎትና በክርስቶስ አንድ ከሆንበት የትዳር አጋራችን ጋር ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል በውስጣችን ያለውን መንፈስ ሳናሳምረው - ሳናስውብ - ሳናጠነክረውም ‹‹እንዲህ ያለ የተቀደሰ ሕይወት ስለምን አልመራም/አልኖርኩም›› ማለት አይገባንም፡፡
- በፊታችን ላይ መልካም ፈገግታን መላበስም ሕይወታችን ደስታን የተመላ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በተቻለን መጠን በትዳር ሕይወታችን በደስታና በሰላም ለመኖር ይረዳን ዘንድ በፊታችን ላይ ፈገግታ እንዲነበብ ለማድረግ መጣጣር ይኖርብናል፡፡ ‹‹ደስ ያለው ልብ ፊትን ያበራል በልብ ኀዘን ግን ነፍስ ትሰበራለች፡፡›› <u>*ምሳ 15፡13፡፡*</u>

<u>*ዘወትር መልካም ፈገግታን የተላበስን የሚያደርጉን ጥቂት ምክሮችን እነሆ፡-*</u>

- እግዚአብሔር በርሱ የደስታን ሕይወት እንመራ ዘንድ ስለሰጠን በማመስገን እንኑር፡፡
- በኛ ያለ ፈገግታ በእግዚአብሔር አማካይነት ከእኛ ለትዳር አጋራችን እንዲደርስ የተሰጠ ልዩ ስጦታ እንደሆነ እናስታውስ፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13

## ደስታ

***ዘወትር መልካም ፈገግታን የተላበስን የሚያደርጉን ጥቂት ምክሮችን እነሆ፡-***

- *ምንም ዓይነት ችግር ቢገጥመን ጌታችን አምላካችን ክርስቶስ እንደሚቆጣጠረውና ነገሩ ሁሉ ለእኛ ጥቅም ይሆን ዘንድ እንደሚመረምረው ብሎም እንደሚያረጋግጥልን እንመን፡፡*
- *ስለ ውስጥ ስሜታችንና ሐሳባችን ከትዳር አጋራችን ጋር እንነጋገርበት፡፡ እግዚአብሔር እርስዋን/እርሱን ረዳት ይሆን/ትሆን ዘንድ ያግዘን/ታግዘን ዘንድ እንደፈጠረልን እናስተውል፡፡*
- *እግዚአብሔር እንደሚወደን በኛና በትዳር አጋራችንም ውስጥ ዘወትር እንደሚኖር እናስታውስ፡፡ ዘፍጥ 18፡15፣ ዘፍጥ 21፡6፣*
- *ፈገግታ (ሳቅ) በተፈጥሮው የሚመነጨው ጊዜን በጸሎት፣ ቅዱሳት መጻሐፍትን በማንበብ ወይም ቅዳሴ በማስቀደስ ከእግዚአብሔር ጋር ከመውሰድ ነው፡፡ ረጅም ጊዜያትን ከጌታችን ጋር ስናሳልፍ እምነታችን ይጠነክራል፣ እምነታችን ከጠነከረም ማንኛውንም አስቸጋሪ ሁኔታ በጽንዓትና በደስታ ተጋፍጠን ማሸነፍ እንችላለን፡፡*
- ፈገግታ/ሳቅ ከፊታችን እንደጠፋ ሆኖ ሲሰማን፤ ቁጥራቸው በርካታ በሆኑ ዓለማዊ ጉዳዮች ራሳችንን ወጥረን እያስጨነቅን ሊሆን ስለሚችል ጥቂት እረፍት ለማድረግ ዘወር ብለን ወደ ገዳማት ለመሄድም ሆነ እረፍትም ለመውሰድ ጥረት እናድርግ፡፡

# <u>የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 13</u>

**ደስታ**

***<u>ዘወትር መልካም ፈገግታን የተላበስን የሚያደርጉን ጥቂት ምክሮችን እነሆ፡-</u>***

- መሳቅ/ፈገግታ መስጠት ሲከብደን የደስታን ሕይወት አቅም መልሰን በውስጣችን ለማግኘት ስለሚረዳን ረጅም ጊዜያትን ለጸሎት መድበን እንጸልይ፡፡
- በሳቅና/ፈገግታ ሆነን የትዳር አጋራችንን መገናኘት ፍቅርን መመጋገብ እንደሆነ እንረዳ፡፡
- ከትዳር አጋራችን ፊት ሳቅ/ፈገግታ እንደጠፋ ሲሰማን መልሰን ለማምጣት የተቻለንን ሁሉ ጥረት እናድርግ፡፡ እግዚአብሔርም የሕይወት አጋርና ረዳት ከሆንነው ከእኛ የሚጠብቀው ይህንኑ ነውና፡፡
- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ባስተማረውና እንዲጽፍም መርቶ ቅዱስ ጳውሎስ በጻፈልን መልዕክት እንደነገረን መደሰት ትእዛዝ እንደሆነ ልብ እንበል፡፡ ‹‹ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ፥ ደስ ይበላችሁ፡፡›› *<u>ፊል 4፡4፡፡</u>* ‹‹አፍህን እንደ ገና ሳቅ ይሞላል፥ ከንፈሮችህንም እልልታ ይሞላል፡፡›› *<u>ኢዮ 8፡21፡፡</u>*
- ‹‹እኛ ግን ነፍሳቸውን ሊያድኑ ከሚያምኑቱ ነን እንጂ ወደ ጥፋት ከሚያፈገፍጉ አይደለንምና፡፡›› *<u>ዕብ 10፡39፡፡</u>* **የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… ትምህርት ተጀምሮ ተፈጸመ፡፡ አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን፡፡ አሜን!!!**

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል፡፡
አሜን፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org